| | |
|---|---|
| ዐይነት ፤ | ዐምደኛ ፡ ድርሰት ። |
| ርእስ ፤ | "ጦማረ ፡ ክዋኔ ፥ 1ኛ ፦ ሀገራዊ ፡ እግዚእናችንን ፡ እናስከብር !" |
| ደራሲ ፤ | "ሥልጡንሕዝብና" ፡ መዜንው ። |
| ዕለት ፤ | መስከረም ፡ 2017 ፡ ዓ.ም. ። |
| ዝግጅት ፤ | ፍጹም ። |
| መጽሔት ፤ | "ሥልጡንሕዝብና" ፡ መዜንው ፡ ቍ.2017-001 |
| ማስታወሻ ፤ | "ክዋኔ" ፡ ዐምድ ። |
| ማሳሰቢያ ፤ | |

# ክዋኔ

CONSTITUTION | دستور

*[በዚህ ፡ ዐምድ ፥ ስለ ፡ ክዋኔ ፡ (ወይም ፡ ሕገ ፡ መንግሥት) ፡ ጕዳይ ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ ሐሳቦችና ፡ አስተያየቶች ፡ ይቀርቡበታል ። ]*

ጦማረ ፡ ክዋኔ ፥ 1ኛ ፦

# ሀገራዊ ፡ እግዚእናችንን ፡ እናስከብር !

---

መስከረም ፡ ቀን ፡ 2017 ፡ ዓ.ም. ።

ከኢትዮጵያ ፡ ሕዝብ ፡ አንድያ ፡ ዐላማ ፥ የመዠመሪያው ፡ ረድፍ ፦

ሀገራዊ ፡ እግዚእናችንን ፡ ማስከበር !

ይላል ።

2.1 ፤ ሀገራዊ ፡ እግዚእና ።

እኸላችን ፡ ዘንድ ፡ እኩል ፡ መረዳት ፡ እንዲኖር ፥ የቃላት ፡ ማብራሪያ ፡ ይቅደምልን ።

"ሀገር" ፤ አንድ ፡ ሥልጣኔ ፡ የሰበሰበው ፡ ሕዝብ ፥ በሰፈረበት ፡ ምድር ፡ ላይ ፡ በሥልጣኑ ፡ የመሠረተው ፡ ግዛት ፤ ወይም ፡ በሌላ ፡ አነጋገር ፥ ሀገር ፡ በሕዝብ ፡ እና ፡ በምድር ፡ መዋሐድ ፡ የሚገኝ ፡ ሐራ ፡ ግዛት ፡ ነው ፥ የሀገር ፡ ባለቤት ፡ ሕዝብም ፡ "ዐምሐራ" ፡ (citizenry) ፡ ይባላል ።

"ዐምሐራ" ፤ ቃል ፡ በቃል ፡ ነጻ ፡ ሕዝብ ፥ የሀገር ፡ ባለቤት ፥ ሿሚ ፡ ሻሪ ፤ እግዚእና ፡ ያለው ፡ ሕዝብ ፡ ማለት ፡ ነው ፡ (citizenry) ።

"እግዚእና" ፤ ገዢነት ፡ ማለት ፡ ነው ፡ (sovereignty) ፥ አንድ ፡ ነጻ ፡ ሰው ፡ በራሱ ፡ እና ፡ በንብረቱ ፡ ላይ ፡ ገዢነት ፡ እንዳለው ፡ ኹሉ ፥ አንድ ፡ ነጻ ፡ ሕዝብም ፡ በራሱ ፡ እና ፡ በሀገሩ ፡ ላይ ፡ ገዢነት ፡ አለው ።

"ሀገራዊ ፡ እግዚእና" ፤ አንድ ፡ ነጻ ፡ ሕዝብ ፡ ወይም ፡ ዐምሐራ ፡ በራሱ ፡ ላይ ፡ እና ፡ በሀገሩ ፡ ላይ ፡ ያለው ፡ የገዢነት ፡ ሥልጣን ።

2.2 ፤ ሀገራዊ ፡ እግዚእናችንን ፡ እናስከብር ።

የኢትዮጵያ ፡ ባለቤት ፥ የኢትዮጵያ ፡ ነጻ ፡ ሕዝብ ፡ ወይም ፡ ዐምሐራ ፥ ዛሬ ፡ በጠላት ፡ ጥቃት ፡ ሀገራዊ ፡ እግዚእናው ፡ ተረምርሞበታል ። ባልሠራው ፡ "ሕገ ፡ መንግሥት" ፡ በጕልበት ፡ ተጨቍኖ ፥ ከርስቱ ፡ ተነቅሎ ፦ "የዠርባ ፡ ዐጥንትኽን ፡ እንሰብረዋለን!" ፡ እየተባለ ፡ ይዛትበታል ።

ለግፍ ፡ አልገዛም ፡ ያለው ፡ የኢትዮጵያ ፡ ነጻ ፡ ሕዝብ ፡ በፋኖነት ፡ ተደራጅቶ ፡ ዐርበኝነቱን ፡ ዠምሯል ።


©ኢ.ሀ.ሥ.አ. ፥ 2017 ፡ ዓ.ም. ።

በታሪክ ፡ እንደምናውቀው ፥ ዛሬም ፡ በእውን ፡ እንደምናየው ፥ ፋኖነት ፡ የኢትዮጵያ ፡ ነጻ ፡ ሕዝብ ፡ ክንድ ፡ እንደ ፡ መኾኑ ፡ መጠን ፥ ሕዝብ ፡ እግዚእናውን ፡ ለማስከበር ፡ በሚያደርገው ፡ ስያሳዊ ፡ ትግል ፡ ዋነኛው ፡ መከታው ፡ እና ፡ መመኪያው ፡ ነው ።

በማንኛውም ፡ ጊዜ ፥ በየትኛውም ፡ ዘመን ፥ ሀገራዊ ፡ እግዚእና ፡ የሚከበረው ፡ በውክልና ፡ እና ፡ በውክልና ፡ ብቻ ፡ ነው ፤ ስለዚሀ ፥ ሕዝብ ፡ ተወካዮችን ፡ በሙሉ ፡ ነጻነት ፡ የመወከል ፡ መብቱ ፡ ሊረጋገጥለት ፡ ይገባል ። ፋኖ ፡ ነጻ ፡ በሚያወጣቸው ፡ ቀበሌዎች ፤ ወረዳዎች ፤ አውራጃዎች ፡ እና ፡ ክፍለ ፡ ሀገሮች ፡ ኹሉ ፥ ሕዝብ ፡ በነጻነት ፡ ወኪሎቹን ፡ እየሠየመ ፥ ወደመሸጋገሪያ ፡ መንግሥት ፡ ምሥረታ ፡ ያመራል ። በተወካዮቹም ፡ አማካይነት ፡ ዐዲሱን ፡ የኢትዮጵያ ፡ ሕገ ፡ መንግሥት ፡ (ወይም ፡ ክዋኔ) ፡ ያረቃል ። ያረቀቀውንም ፡ ሕገ ፡ መንግሥት ፡ በሕዝባዊ ፡ ፈረዳ ፡ ሲያጸድቅ ፡ እና ፡ ሥልጡንሕዝባዊ ፡ መንግሥቱን ፡ ሲመሠርት ፥ ያን ፡ ጊዜ ፡ የኢትዮጵያ ፡ ሕዝብ ፡ ሀገራዊ ፡ እግዚእናውን ፡ ያረጋግጣል ።

ይህን ፡ ሥልጡንሕዝባዊ ፡ ኺደት ፡ የምንመራበትን ፡ ስልት ፥ ኢ.ሀ.ሥ.አ. ፡ ያቀረበው ፡—

"ሥልጡንሕዝባዊ ፡ የመሸጋገሪያ ፡ መንግሥት ፡ ሀገራዊ ፡ ቅያስ"

የተሠኘውን ፡ ሰነድ ፡ ለሕዝብ ፡ ስሜት ፡ አቅርቧል ፥ ፈጥነን ፡ ሀገራችንን ፡ እንታደግበት ፡ !

---

ስለኢ.ሀ.ሥ.አ. ፡ አመሠራረት ፡ እና ፡ ስለ ፡ መሠረታውያን ፡ ደንቦቹ ፡ በቂ ፡ መረጃን ፡ ከመርበቢያው ፡ ከ ፡—

www.slttunhzb.net

ማግኘት ፡ ይቻላል ።

ማንኛውም ፡ ኢትዮጵያዊ-ሀገራዊ ፡ የኢ.ሀ.ሥ.አ. ፡ የመብት ፡ አባል ፡ ነው ፤ በመብቱ ፡ መሥራትን ፡ ወይም ፡ አለመሥራትን ፡ የራሱ ፡ ምርጫ ፡ ይወስነዋል ።

---

## የቃላት ፡ መፍቻ ፤

**ሀገራዊ** ፡ ( *ስም* ) ፤ የሀገር ፡ ሠሪ ፥ የሀገር ፡ ባለቤት ፥ ዐምሐራ ፡ (citizen, *n.*)

**ሀገራዊ** ፡ (*ቅጽል*) ፤ የሀገር ፡ (citizen, *adj.*)

**መርበቢያ** ፤ የመረብ ፡ ገጽ ፡ መገኛ ፡ (web ፡ site)

**ሥልጡን** ፤ ሥልጣን ፡ ያለው ፥ የብጤውን ፡ መብት ፡ አክብሮ ፡ የራሱን ፡ መብት ፡ የሚያስከብር ፥ ሥሉጥ ፡ (civil)

**ሥልጡንሕዝባዊ** ፤ የሥልጡንሕዝብ ፡ (democratic)

**ሥልጡንሕዝብ** ፤ ሥልጣን ፡ ያለው ፡ ሕዝብ ፥ የብጤውን ፡ መብት ፡ አክብሮ ፡ የራሱን ፡ መብት ፡ የሚያስከብር ፥ ሥሉጥ ፡ ሕዝብ ፡ (democrat)

**ሥልጡንሕዝብና** ፤ የኢትዮጵያ ፡ ሥልጣኔ ፡ ወይም ፥ አንዱ ፡ የሌላ ፡ ብጤውን ፡ መብት ፡ በማክበር ፡ ወንፈል ፥ ጠቅላላው ፡ ሕዝብ ፡ ዐብሮ ፡ የሚኖርበት ፡ ሥልጡን ፡ ሥርዐት ፡ (democracy)

**ጦማር** ፤ መልክት ፡ (mail ፡ ወይም ፡ post)

**እግዚእና** ፤ ገገርነት ፡ (sovereignty)


©ኢ.ሀ.ሥ.አ. ፥ 2017 ፡ ዓ.ም. ።

**ኢትዮጵያዊ-ሀገራዊ** ፤ የኢትዮጵያ ፡ ሀገራዊነት ፡ ያለው ፡ (Ethiopian citizen)

**ዐምሐራ** ፤ ዐም ፡ = ፡ ሕዝብ ፥ ሐራ ፡ = ፡ ነጻ ፥ በተገናኘ ፡ ነጻ ፡ ሕዝብ ፥ የሀገር ፡ ባለቤት ፥ እግዚእና ፡ ያለው ፥ የሀገር ፡ ሠሪ ፥ ሀገራዊ ፡ ሕዝብ ፡ (citizenry)

**ዐምሐራዊ** ፡ ( *ስም* ) ፤ የዐምሐራ ፡ አባል ፥ ሀገራዊ ፡ (citizen, *n.*)

**ዐምሐራዊ** ፡ ( *ቅጽል* ) ፤ የዐምሐራ ፥ ሀገራዊ ፡ (citizen, *adj.*)

**ስያስ** ፤ ዘዴ ፡ (policy)

**ስያሳ** ፤ "ፖለቲካ" ፡ (politics)

**ስያሳዊ** ፤ "ፖለቲካዊ" ፡ (political)


©ኢ.ሀ.ሥ.አ. ፥ 2017 ፡ ዓ.ም. ።